## መታሠቢያነቱ

“ሖሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ ዓፅናፈ ዓለም” ተብለው አምላካዊውን ቃል ጠብቀው በወንጌል መልዕክት ለተሠማሩ በእግረ ሐዋርያት ለተተኩ ለአባቶቼና ለወንድሞቼ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሠባኪያነ ወንጌል ይሁንልኝ።

“ሰው ሰውን ቢበድለው ስለ እርሱ እግዚአብሔር ይፈርድለታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለእግዚአብሔር ማን ይከራከርለታል?” (1ኛ ሳሙ 2 ፥ 25 )

ያለደራሲው ፈቃድ ውጪ ማንም ሰው ሊያባዛና ሊያትም የተከለከለ ነው።
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All right reserved.

## ማውጫ

ገጽ

1· መግቢያ ........ 5
2· ቤተክርስቲያን ........ 7
3· የአትል ልማድና የባሕል ገጽታ በቤተክርስቲያን ........ 9
4· ካቴድራል ........ 12
5· ደብር ........ 13
6· ገዳም ........ 14
7· የቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ........ 15
8· የሳሎ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (አቃቂ) ........ 16
9· ርዕሰ አድባራት መንበረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን (እንጦጦ) ........ 17
10· ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያን (ካሳንቺስ) ........ 18
11· ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን (እንጦጦ) ........ 19
12· ጽርሃ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን ( ) ........ 20
13· ደብረ መንክራት ሥዕል ቤት ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን (ፊት በር) ........ 21
14· መካነ ሥላሴ በዓለወልድ ቤተክርስቲያን (4 ኪሎ) ........ 22
15· ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (አራዳ) ........ 23
16· መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ግቢ) ........ 24
17· ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን (መርካቶ) ........ 25
18· መካነ ሠማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን (ለገሃር) ........ 26
19· ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስቲያን (ጉለሌ) ........ 27
20· ሐመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን (እንጦጦ) ........ 28
21· ደብረ ሰላም ቀጨኔ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ቀጨኔ) ........ 29
22· ደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተክርስቲያን (መሣለሚያ) ........ 30
23· መካነ ሕይወት አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን (ፈረንሳይ) ........ 31
24· ደብረ ሠላም እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን (አቢዮት) ........ 32

www.ethiopianorthodox.org

25· ታዕካ ነገሥት በዐታ ማርያም ቤተክርስቲያን (ፊት በር) ........................ 33
26· ደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን (ጉተራ) ........................ 34
27· ደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን ........................ 35
28· ገነተ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን (ፈረንሳይ) ........................ 36
29· መንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን (6 ኪሎ) ........................ 37
30· ማህደረ ስብሐት ልደታ ቤተክርስቲያን (ሜክሲኮ)........................ 38
31· መንበረ መንግሥት ቊስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን (ቊስቋም)........................ 39
32· ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል (የካ) ቤተክርስቲያን (ሾላ) ........................ 40
33· መንበረ ፓትርያሪክ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን (5 ኪሎ) ........................ 41
34· መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን (4 ኪሎ) ........................ 42
35· ጽርሃ ንግሥት ፋሪ ሐና ማርያም ቤተክርስቲያን (ፋሪ) ........................ 43
36· ወይብላ ማርያም ቤተክርስቲያን (ፈረንሳይ) ........................ 44
37· ጽርሃ ጽዮን ሐዋርያት ጎላ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ቸርቸል) ........................ 45
38· ሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን (ኮልፌ) ........................ 46
39· ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (6 ኪሎ) ........................ 47
40· ረቢ መካነ ጎልጎታ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ካራ ቆሬ) ........................ 48
41· መንበረ ስብሐት ሥላሴ ቤተክርስቲያን (እንጦጦ) ........................ 49
42· ደብረ ክዋክብት ገ/ክርስቶስ ወአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን ........................ 50
43· ደብረ ኃይል ራጉኤል ቤተክርስቲያን (መርካቶ) ........................ 51
44· ደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተክርስቲያን (ጉተራ) ........................ 52
45· መካነ ጎልጎታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን (ዮሐንስ) ........................ 53
46· ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ክፍለሃገር መናኸሪያ) ........................ 54
47· መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ጎፋ) ........................ 55
48· መንበረ ሕይወት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ለቃቂ) ........................ 56
49· ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ሣር ቤት) ........................ 57
50· መካነ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (ቃሊቲ) ........................ 58
51· ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ቦሌ) ........................ 59
52· እንቀፀ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ፈረንሳይ ጫቁኑ) ........................ 60
53· ደብረ ምጥማቅ ሠዓሊተ ምሕረት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን
(ላምበረት)........................ 61
54· ደብረ ምሕረት ወህኒ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ወህኒ ቤት ውስጥ) ........................ 62
55· ደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን (አዲሱ ገበያ) ........................ 63
56· ደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (አስኮ) ........................ 64
57· ዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ልዑል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ኮተቤ) ........................ 65
58· ደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (ገርጂ) ........................ 66
59· ደብረ ሣሌም መድኃኔዓለም መጥምቁ ዮሐንስ ወአቡነ አረጋዊ
ቤተክርስቲያን (ቦሌ) ........................ 67
60· ምዕራፈ ቅዱሳን ፈለገ ሕይወት ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን (ሣሪስ) ........................ 68
61· መካነ ቅዱስን ኢያቄም ወሐና ቤተክርስቲያን (ኮተቤ) ........................ 69
62· ምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን (ሣሪስ) ........................ 70
63· ደብረ ምጥማቅ ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ቤተክርስቲያን
(ኮልፌ አጠና ተራ) ........................ 71
64· ደብረ መንክራት ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን (ኮልፌ አጠና ተራ) ........................ 72
65· ደብረ ይድራስ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (አውጉስታ) ........................ 73
66· ደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ላፍቶ) ........................ 74
67· ደብረ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (የካ) ........................ 75
68· ገዳመ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን (መሣለሚያ) ........................ 76
69· ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (ፈረንሣይ) ........................ 77
70· ቤዛ ብዙኃን ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን (ጎፋ) ........................ 78
71· ምዕራፈ ፃድቃን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን (መካኒሣ) ........................ 79
72· ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (የልደታው) ........................ 80
73· ደብረ ምፅላል እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን (ላምበረት) ........................ 81

www.ethiopianorthodox.org

74· አንቀፀ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (አየር ጤና) ..................... 82
75· ደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (መካኒሣ) ..................... 83
76· ደብረ ጽባሕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ሣጠራው) (CMC) ............. 84
77· ደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ቃሊቲ) ..................... 85
78· ደብረ ዕንቁ ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን (ሩሲያ ኤንባሲ) ..................... 86
79· ደብረ ገነት ፉሪ ዕንቁ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ፉሪ) ..................... 87
80· ብሔረ ጽጌ ማርያም ቤተክርስቲያን (ብሔረ ጽጌ) ..................... 88
81· ምስራቀ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (መካኒሣ) ..................... 89
82· ወይብላ ማርያም ቤተክርስቲያን (ቀራንዮ ሠፈር) ..................... 90
83· የደብረ ቅዱስ ደብረ ቀርሚሎስ ካራአሎ መድኃኔዓለም ወአቡነገሪማ
(ካራአሎ) ..................... 91
84· የሐመረወርቅ ማርያም ቤተክርስቲያን (ሣሪስ) ..................... 92
85· የቀጨኔ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ቀጨኔ) ..................... 93
86· የደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ታጠቅ) ..................... 94
87· የጋራ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን (የካ ጋራ) ..................... 95
88· የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ቄራ) ..................... 96
89· የካ ጋራ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ..................... 97
90· የቦሌ ቡልቡላ ደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ..................... 98
91· ማጠቃለያ ..................... 99
92· በጥናት ሥራዬ ላይ የተጠቀምኩባቸው ምንጮች ..................... 100
93· የአብያተክርስቲያኑን አድራሻ የሚያሳይ ልዩ ሠርጠረዥ ..................... 103



[stamp]

## መግቢያ


የመጻሕፍትና የመጽሔቶችን ምሥጢራዊ መልዕክት በመጠኑ በመግለጽ ረገድ የመግቢያ ጽሁፍ ታላቅ ድርሻ አለው። በተለይም አንባቢያን በስሜት ተመስጠው ወደ ቁም ነገር መልዕክቱ እንዲገቡ መግቢያ የሚገፋፋ ቀስቃሽ መልዕክት ነው። እኔም በእዚይች መጠነኛ ቁም ነገር አዘል መልዕክት የመጀመሪያ እጅ መፍቻ መጽሐፍ አዘጋጅቼ ይዘቱን በዚህ የመግቢያ መልዕክት ጥቂት ግንዛቤን አስጨብጬ ውስጣዊ ይዘቱን በተመለከተ ግን አንብቦ በመረዳት የታሪክ የኃይማኖት የሃገር ፍቅር ላለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቀርባለሁ።

ይህ ፍኖተ ቤተክርስቲያን በመባል የተሠየመው መጽሐፍ በነገረ መለኮት ላይ ያላተኮረ ሆኖ በታሪክና በትውፊት፣ በመረጃ ጥንቅር ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም በመንፈስ ቅዱስ አሣሣቢነት ይህን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ፈቃዱ ሆኖ ሁሉን ያደረገልኝ አምላኬን ልዑል እግዚአብሔርን አመሠግናለሁ።

መጽሐፍ ስለዓለም የምናውቅበት መሣሪያ ነው። በመጽሐፍት ላይ ሁሉ ነገር ስለሚገለጹ ዓለምን በንባብ ሕሊና ቁጭ ብሎ በውስን ስፍራ መመልከት ይቻላል መጻሕፍት ምስጢራት የሚገኙባቸው ታሪክን ለትውልድ ጠብቀው የሚያስተላልፉ መካሪ፣ አጽናኝ ተስፋ ሰጪ ስሜትን በአዲስ መንፈስ ቀስቀሰው የሚያነቃቁና የሰጧቸውን ተቀብለው አደራ የሚጠብቁ ከመሆናቸውም በላይ በእጅት የሚገርመውና የሚያስደንቀው መጽሐፍት ገልጠው ሲያነቧቸው ውለው ተሰልችተው ሳይከድኗቸው ተጥለው ቢሄዱና ተመልሰው መጥተው ቢያነቧቸው ቀር የማይሰኙ፣ የማይሰለቹ እውነተኛ ወዳጆች ናቸው። እኔም ይህን መጽሐፍ ሳዘጋጅ የነበረኝ ጽኑ ፍላጐትና ስሜት ለዓላማዬ መሳካት ታላቅ አስተዋፅኦ ቢያደርግልኝም ይህ መጽሐፍ አንድ ቦታ ቁጭ ብሎ የሚዘጋጅ የሕሊና ውጣ ውረድን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ብዙ መኳዝና ብዙ ድካም የሚጠይቅ ነው። ይሁን እንጂ ለመጀመር ልቦናዬን ቀስቀሶ ያስጀመረኝ አምላኬ አስፈጽሞኛል።

www.ethiopianorthodox.org


## የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
## (ገዳም) (ግቢ)
## ከ1889 –1991 ዓ.ም. = የ102 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 14 ቀበሌ 18 ክሬት በር ቤተመንግሥት አጠገብ የሚገኘው የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተምስራው አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ1.6 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። በ1889 ዓ.ም. ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥራል። መንበረ መንግሥት ተብሎ የተሰየመው በቤተመንግሥቱ አጠገብ ስለሚገኝ ነው። ገዳሙ በመምህር ይተዳደራል።



## የደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን
## (ደብር) (መርካቶ)
## ከ1898 –1991 ዓ.ም. = የ93 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 3 ቀበሌ 31 ሱማሌ ተራ አካባቢ ወይም መርካቶ መግቢያው ላይ የዳግሚት ደብረ ሊባኖስ ደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በደብሩ ምዕራብ አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ2.9 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። በ1898 ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥራል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን (ደብር) (ሣሪስ መንገድ)

### ከ1911 – 1991 = የ80 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 19 ቀበሌ 54 ከነተራ በታች ብሔረ ጽጌ መናፈሻ ማዞሪያ ላይ የሚገኘው የብደረ ናዝሬት የቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ9·1 ኪ·ሜ· ርቀት አለው። ደብሩ በ1911 ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥሯል። ደብረ ናዝሬት ተብሎ የተሠየመው ናዝሬት ጌታ ያደገባት አረጋዊው ቅዱስ ዮሴፍ የተቀመጠባትና ብዙ ምስጢራት የተገለፀባት ቦታ በመሆኗ ደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ተብሎ ተሰይሟል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ነጎድጓድ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1914 – 1991 = የ77 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 1 ቀበሌ 03 አስኮ በሚወስደው መስመር አባ ኮራን ሰፈር ተብሎ በሚጠራል አካባቢ የሚገኘው የደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንሰ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተምዕራብ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ3·6 ኪ·ሜ· ርቀት አለው። ደብሩ በ1914 ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥሯል። ደብረ ነጎድጓድ ተብሎ መሰየሙ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ (የነጎድጓድ ልጅ) ተብሎ ስለሚጠራ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1916 – 1991 = የ75 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 22 ቀበሌ 04 ከሜክሲኮ አደባባይ በታች ባልቻ ሆስፒታል ፊት ለፊት የሚገኘው የማኅደረ ስብሃት ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ6·8 ኪ·ሜ· ርቀት አለው። ደብሩ በ1916 ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥሯል። ማህደረ ስብሃት ተብሎ የተሠየመው ማህደር ሲል ማደሪያ ስብሃት ሲል ምስጋና ለማለት ነው። ይህም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በፍጥረታት ሁሉ ለሚመሰገነው አምላክ ማደሪያ ሆና ስለተገኘች ማህደረ ስብሃት ተብላ ደብሩ ስያሜ ተሰጥቶታል። በመምህር ይተዳደራል።





## መንበረ ንግስት ቁስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1919 – 1991 = የ72 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 11 ቀበሌ 01 ከሸርሜዳ በላይ 17 ቁጥር ማዞሪያ አካባቢ የሚገኘው የመንበረ ንግስት ቁስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ7·8 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ መንበረንግስት ቁስቋም ተብሎ የተሰየመው ንግስት ዘውዲቱ ስለአሠሩት መንበረ ንግሥት ሲባል ቁስቋም የተራራ ስም ናት ግብፅ ውስጥ እመቤታችን በስደት ጊዜዋ ያረፈችባት የተገለፀችባት ቅድስት ደብር ናት ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የረቢ መካነ ጎልጎታ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ደብር) (ካራ ቆሬ)

### ከ1936 – 1991 = የ55 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 24 ቀበሌ 16 ጅማ በር ካራ ቆሬ ሰፈር የሚገኘው የረቢ መካነ ጎልጎታ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ13·9 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1936 ዓ·ም· ተመስርቶ ረጅም እድሜን አስቆጥሯል። ረቢ መምህር ማለት ሲሆን በእብሪይስጡ ረቡኒ ብሎ መምህር ይለዋል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።




www.ethiopianorthodox.org



## የመንበረ ስብሐት ሥላሴ ቤተክርስቲያን (ደብር)


### ከ1937 – 1991 = የ54 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 11 ቀበሌ 02 ከሽሮ ሜዳ በላይ የሚገኘው የመንበረ ስብሃት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተሰሜን አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ5·9 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1937 ዓ·ም· ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥሯል። መንበረ ስብሃት ተብሎ የተሰየመው መንበር ማክበሪያ ማደሪያ ሲሆን ስብሐት ምስጋና ማለት ነው። ሥሉስ ቅዱስ በረድኤት አድረው የሚመሠገኑበት የሚወደሠበት ደብር በመሆኑ ነው። ለደብሩ አለቃ የተሰጠ የሥልጣን ስም መልአክ ስባሄ ሲባል ይህም አስወዳሽ አስመስጋኝ መልአክ ለማለት ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

## የደብረ ከዋክብት ቅዱስ ገብረክርስቶስ ወአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን (ደብር)

## ከ1942 –1991 ዓ.ም. = የ49 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 23 ቀበሌ 16 በ3 ቁጥር መስመር ዘነበወርቅ ሆስፒታል አካባቢ የሚገኘው የደብረ ከዋክብት ቅዱስ ገብረክርስቶስ ወአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትሪያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ9.6 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። በ1942 ተመስርቶ ረዥም እድሜን አስቆጥሯል። ደብረ ከዋክብት ተብሎ መሰየሙ ፀሐይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጨረቃ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት በከዋክብት ይመሰላሉና ደብሩ ደብረ ከዋክብት ተብሎ ተሰይሟል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (መርካቶ)

## ከ1948 – 1991 = የ43 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 5 ቀበሌ 06 መሐል መርካቶ ውስጥ የሚገኘው የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ2·3 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1948 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ኃይል ተብሎ የተሰየመው መላእክት በባሕሪያቸው ኃያላን ረቂቃን በመሆናቸው ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተክርስቲያን
## (ደብር)

### ከ1948 – 1991 = የ43 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 14 ቀበሌ 49 በጎተራ መስመር አካባቢ የሚገኘው የደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ7·1 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1948 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ይባቤ ተብሎ የተሰየመው ይባቤ ማለት ምስጋና ማለት ሲሆን ቅዱስ ያሬድ በጥዑም ዜማው ፈጣሪውን እያመሰገነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዜማ ምስጋና ደራሽ በመሆኑ ደብሩ ደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ተብሎ ተሰይሟል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የመካነ ጎልጎታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን
## (ደብር)

### ከ1950 – 1991 = የ41 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 1 ቀበሌ 03 አባኰራን ሰፈር ዮሐንስ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ የምትገኘው የመካነ ጎልጎታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ3·6 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1950 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደብሩ መካነ ጎልጎታ ተብሎ መሠየሙ መካን ሲል ቦታ ጎልጎታ ሲል ኢየሩሳሌም ውስጥ ያለ የተራራ ስም ነው። በዚህም ቦታ እመቤታችን ቅድስት ድንግል የጸለየችበትና የባረከችው ቦታ ነው። ደብሩ በዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን ሰበካ ስር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ካቴድራል) (አዲሱ ሚካኤል)

### ከ1953 – 1991 = የ38 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 7 ቀበሌ 31 ከክፍለ ሀገር አውቶቢስ መናኻሪያ ጀርባ የሚገኘው የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ4·1 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1953 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን (ካቴድራል) (ጎፋ)

### ከ1955 – 1991 = የ36 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 20 ቀበሌ 53 በቄራ መስመር 34 ቁጥር ማዞሪያ አካባቢ ጎፋ ሰፈር የሚገኘው የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ10 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1955 ዓ·ም· ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። መካነ ሕያዋን (የሕያዋን ቦታ) በማለት ካቴድራሉ ስያሜ ተሰጥቶታል። በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የመካነ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (ደብር) (ቃሊቲ)

### ከ1958 – 1991 = የ33 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በልዩ ክፍተኛ 2 ቀበሌ 08 የሚገኘው የመካነ ሕይወት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ20 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1958 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልገሎት እየሰጠ ነው። መካነ ሕይወት ተብሎ መሰየሙ መካን ሲል ቦታ በጥቅሉ ምካነ ሕይወት ብሎ የሕይወት ቦታ ለማለት ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።



## የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (ቦሌ)

### ከ1968 – 1991 = የ23 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 17 ቀበሌ 20 ቦሌ ሩዋንዳ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ11·2 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1968 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልገሎት እየሰጠ ነው። ደብረ ምሕረት ተብሎ መሰየሙ ቅዱስ ሚካኤል የምሕረት የይቅርታ መልአክ በመሆኑ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

ፍኖት ሪቃና ቤት
የግል ቤተ

## የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (ወህኒ ቤት)

### ከ1969 – 1991 = የ22 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 21 ቀበሌ 19 ወህኒ ቤት (አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት) ግቢ ውስጥ የሚገኘው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ5·2 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብረ ምሕረት የተባለው ቅዱስ ሚካኤል የምሕረት የይቅርታ መልአክ ስለሆነ ነው። ደብሩ በ1969 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደብሩ በመምህር የተዳደራል።





## የደብረ ሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን (ደብር)


### ከ1969 – 1991 = የ22 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 10 ቀበሌ 22 ከሰሜን ማዘጋጃ ቤት በላይ አልፎ በተለምዶ መርሀቤቴ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የደብረ ሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ4·8 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1969 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ሲና ተብሎ የተሰየመው ሲና የተራራ ስም ሲሆን ቅዱስ እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ እየተገለፀ እንዳነጋገረው ለመግለጽ ነው። በመሆኑም ደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ተብሎ ተሰይሟል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
## (ደብር) (አስኮ)
## ከ1969 – 1991 ዓ.ም. = የ22 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 8 ቀበሌ 22 በወለጋ መስመር አስኮ፣ ጉለሌ ሰፈር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የደብረ ገነት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተምዕራብ አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ10 ኪ.ሜ. ርቀት አለው። በ1969 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ሲገኝ ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ልዑል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
## (ደብር) (ኮተቤ)
## ከ1969 – 1991 = የ22 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 1 ልዩ ቀበሌ 03 ኮተቤ አካባቢ 57 ቁጥር ማዞሪያ ላይ የሚገኘው የደብረ ልዑል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነው። ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ14.1 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። በ1969 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ልዑል ተብሎ የተሰየመው የልዑሉ የቅዱስ ገብርኤል ደብር ለማለት ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (ደብር) (ገርጂ)

### ከ1972 – 1991 = የ19 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 17 ቀበሌ 25 መገናኛን አልፎ ገርጂ ሠፈር የሚገኘው የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተምሥራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጽ/ቤት በ15·3 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1972 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ ደብረ ገነት ተብሎ በመሰየም በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቁ ዮሐንስ ወአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን (ደብር) (ቦሌ)

### ከ1972 – 1991 = የ19 ዓመት ታሪክ




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 17 ቀበሌ 23 ቦሌ ክፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠገብ ወይም 9 ቁጥር ማዞሪያ አካባቢ የሚገኘው የደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ10 ኪ.ሚ. ርቀት ላይ ይገኛል ። ደብሩ በ1972 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ሳሌም ተብሎ መሠየሙ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ጌታውን እየመራ በሄኖን በመቁሩብ ሳሌም በማየ ዮርዳኖስ እንዳጠመቀው ለመግለጽ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም መጥምቁ ዮሐንስ ወአቡነ አረጋዊ ተብሎ ተሰይሟል። በመምህር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (ላፍቶ)

### ከ1983 – 1991 = የ8 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 19 ቀበሌ 58 ከብሔረ ጽጌ ማርያም ማዶ ጋሬው ላይ የሚገኘው የደብረ ትጉሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ13·8 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1983 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ትጉሃን ሲል መላእክት ለምስጋናና የሰው ልጆችን ለመጠበቅ የተጉ በመሆናቸው ደብረ ትጉሃን ተብሎ ተሰይሟል። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (ደብር) (የካ)

### ከ1983 – 1991 = የ8 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 16 ቀበሌ 22 ኮተቤ ብረታ ብረት ፋብሪካ ጀርባ የምትገኘው የደብረ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ነው። በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ11·5 ኪ·ሜ· ርቀት አለው። በ1983 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብረ ምሕረት የተባለው ኪዳነ ምሕረት የምሕረት ቃል ኪዳን ስለተሰጣት ለመግለጽ ደብሩ ደብረ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ተብሏል። በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የገዳመ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን (ገዳም)

### ከ1983 – 1991 = የ8 ዓመት ታሪክ



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 24 ቀበሌ 12 ከአማኑኤል ቤተክርስቲያን ወንዙን ማዶ አልፎ የሚገኘው የገዳመ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ7·8 ኪ·ሜ· ርቀት አለው። ገዳሙ በ1983 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ገዳሙ በመምህር ያተዳደራል።





## የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን (ደብር) (ፈረንሳይ)

### ከ1983 – 1991 = 8 ዓመት




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 12 ቀበሌ 12 ከፈረንሳይ ኤምባሲ በላይ የሚገኘው የደብረ ፀሐይ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው። በስተ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ8·9 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1983 ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የአንቀጸ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1985 – 1991 = 6 ዓመት



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 24 ቀበሌ 15 አየር ጤና በተስምዶ ኮምቤ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የአንቀጸ ምሕረት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ13 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። በ1985 ተመስርቶ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (መካኒሣ)

### ከ1985 – 1991 = 6 ዓመት




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 23 ቀበሌ 14 መካኒሣ ሰፈር የሚገኘው የደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ11·1 ኪ.ሜ. ርቀት አለው። ደብሩ በ1985 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ዕንቁ ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን
## (ደብር)

ከ1986 1991 = 5 ዓመት



ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 12 ቀበሌ 21 ከራሺያ ኤምባሲ ጀርባ ጋራው ላይ የሚገኘው የደብረ ዕንቁ ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ነው። በስተሰሜን አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ6 ኪ.ሜ. ርቀት አለው። በ1986 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የደብረ ገነት ፉሪ ዕንቁ ገብርኤል ቤተክርስቲያን
## (ደብር)

ከ1986 – 1991 = 5 ዓመት

ይህ ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ በገበሬ ማኀበር ክልል ውስጥ የሚገኘው የደብረ ገነት ዕንቁ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ24 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል። በ1986 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።



www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (ታጠቅ)

**ከ1979 – 1991 = 17 ዓመት**

ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 24 ቀበሌ 19 ከወይብላ ማርያም ቤተክርስቲያን ማዶ በኮልፌ አቀጣጫ የሚገኘው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። በስተምዕራብ አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ14 ኪ.ሜ. ርቀት አለው። በ1979 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።






## የተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን (ደብር) (ጋራ ተክለሃይማኖት)

**ከ1978 – 1991 = 13 ዓመት**

ከቀሻው በ12ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ሲሆን ይህ አዲሱ ቤተክርስቲያን በቅርብ ጊዜ የተሠራ ነው።




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 17 ቀበሌ 21 ከየካ ሚካኤል ጀርባ ጋራው ላይ የሚገኘው ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን ነው። በስተምስራቅ አቀጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የ8 ኪ.ሜ. ርቀት አለው። ደብሩ በ1978 ዓ.ም. ተመስርቶ ረጅም እድሜን አስቆጥረው ከሚገኙት ጥንታውያን ቤተክርስቲያን አንዱ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የደብረ ምሕረት ሚካኤል ቤተክርስቲያን (ደብር) (ከወህኒ ውጪ)

### ከ1987 – 1991 = 2 ዓመት




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በክፍተኛ 21 ቀበሌ 19 ከወህኒ ቤቱ ጀርባ የሚገኘው የደብረ ምሕረት ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። ደብሩ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ7·4 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። በ1989 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## የካ ጋራ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1990 – 1991 = 1 ዓመት




ይህ በአዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ 16 ቀበሌ 22 ከየካ ኪዳነ ምሕረት ማዶ ከተራራው ጫፍ ላይ የሚገኘው የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ነው። በስተምስራቅ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ11 ኪ·ሜ· ርቀት ላይ ይገኛል። ደብሩ በ1990 ዓ·ም· ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እያበረከተ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።

www.ethiopianorthodox.org

## የቦሌ ቡልቡላ ደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን (ደብር)

### ከ1990 – 1991 = 1 ዓመት



ይህ ከአዲስ አበባ ከተማ ወጣ ብሎ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ቦሌ ቡልቡላ በሚባለው አካባቢ የሚገኘው የደብረ ገነት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ነው። ደስተደቡብ አቀጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በ13 ኪ.ሚ. ርቀት ላይ ይገኛል። በ1990 ዓ.ም. ተመስርቶ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ደብሩ በመምህር ይተዳደራል።





## ማጠቃለያ

ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለእርሱ የሆነ የለም (ዮሐ. 1/3) በማለት ሥራን ለማሠራት አነሣስቶ ማስጀመርም ሆነ ማስፈፀም የእርሱ ፈቃድ የሆነ አምላክ ይህን መጠነኛ ጽሑፍ አስጀምሮ ስለአስፈፀመኝ ፈጣሪዬ የተመሠገነ ይሁን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሠፊው የተመለከትናቸው አብያተ ክርስቲያናት ብዛታቸው 84 የሆነው በነጠላ ቁጥር ቆጥረን ነው። ማለትም በአንድ ሰበካ ጉባኤ ስር የሚተዳደሩ ሁለት የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። እነዚህንም ከዚህ ቀጥለን አስቀምጠናቸዋል።

1ኛ. መካነ ሥላሴ ባዕለወልድ ቤተክርስቲያን በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ሠበካ ሥር ይተዳደራል።
2ኛ. የደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ሥር ይተዳደራል።
3ኛ. የደብረ መንክራት ስዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን በታዕካ ነገሥት በዐታ ማርያም ገዳም ሰበካ ሥር ይተዳደራል።
4ኛ. የወይብላ ማርያም ቤተክርስቲያን በገነተ ኢየሱስ ገዳም ሰበካ ሥር ይተዳደራል።
5ኛ. የደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በደብረ ሰላም ቀጨኔ መድኃኔዓለም ሰበካ ሥር ይተዳደራል።
6ኛ. የምዕራፈ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን በምዕራፈ ቅዱሳን ፈለገ ሕይወት አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ሠበካ ሥር ይተዳደራል።
7ኛ. የመካነ ጎልጎታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተክርስቲያን ሠበካ ሥር ይተዳደራል።

እነዚህ በዝርዝር የገለጽናቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት በጠቀስናቸው ሰበካ ሥር የሚተዳደሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 77 አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ቋሚ የሰበካ ጉባኤ አላቸው። በአዲስ አበባ ከተማ ካሉት 84 አብያተ ክርስቲያናት አንድ ክፍለ ዘመን (መቶ ዓመት) ሞልቶት በቀርስነት ያሉትን ከበስተጀርባ ካስቀመጥነው የትክል ዘመን ቁጥር ጋር በማቀናነስ አንባቢያን ሊያውቁት ይችላሉ። ለምሣሌ የደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያንን ብንጠቅስ 1991 – 1875 = 116 የአንድ መቶ አስራ ስድስት ዓመት እድሜ ያለው ሲሆን ከአንድ ክፍለ ዘመን (ከመቶ ዓመት በላይ በመሆኑ በቀርስነት ከተመዘገቡት ጥንታዊያን አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው።)



www.ethiopianorthodox.org

## ልዩ ምስጋና

ከሁሉ በላይ ፈቃዱ ሆኖ ሥራዬን አስጀምሮ ላስፈጸመኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው።

እንዲሁም በጽሕፈት ሥራ ላይ በኮምፒውተር አገልግሎት ለረዳችኝ ለወ/ሮ አስራቴነሽ ከበደ በይበልጥ የዓላማዬን በጎነትና ድካሜን አይተውልኝ የዋጋ ቅናሽ በማድረግ ያተሙልኝን አቶ ሰሎሞን ታደሰንና ቀሲስ ኃይለገብርኤልን በአጠቃላይ በዚህ ሥራዬ ላይ ቀን ትብብራቸው ያልተለየኝ ወንድሞቼንና አባቶቼን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የማያልፍ የዘላለም መንግስቱን እንዲያወርስልኝ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልኝ።

www.ethiopianorthodox.org

